# የታቀደዉ የአንድነት መስቀል አደባባይ ሕዝባዊ ስብሰባን በተመለከተ

## ልዩ ዘገባ - አወደ ኢትዮጵያ

ግንቦት 15 ቀን 2001 ዓ.ም

አገራዊ አንድነትና ሉዓላዊነት ተጠብቆ፣ ዜጎቹዋ በሰላምና በነጻነት፣ የሰብዓዊና የዲሞክራሲያዊ መብታቸዉ ተከብሮ፣ በእኩልነት የሚኖሩባትን አንዲት ኢትዮጵያ ለመመስረት የሚደረገዉ ትግል፣ ወሳኝ ምእራፍ ላይ መድረሱን የሚናገሩ ጥቂቶች አይደሉም።

በዘጠና ሰባት በተደረዉ ምርጫ ወቅት ወያኔ-ኢሕአዴግ ከምእራባዉያን የሚያገኘዉ ጥቂት እርዳታ እንዳትቀርበት ሲል በከፈተዉ ትንሽ ቀዳዳ፣ አይሎና ገንፍሎ የወጣዉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላማዊ ንቅናቄ እንዳስደነገጠዉና ከድንጋጤዉም የተነሳ ጨካኝ የኃይል እርምጃ በመወሰድ በመቶ የሚቆጠሩ ሰላማዊ ዜጎችን እንደገደለ፣ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩትን እንዳሰረም የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነዉ። ያ የቅንጅት መንፈስ ተብሎ የሚታወቀዉን የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላማዊ ንቅናቄ ለማዳፈንም፣ ወያኔ-ኢሕአዴግ ለአራት አመታት ከፍተኛ ጥረትና ድካም፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ሲያደርግ ቆይቷል።

እንደዚያም ሆኖ ግን የሕዝብ እንቅስቃሴ አልተዳፈነም። በወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የሚመራዉና የቅንጅት ወራሽ የሆነዉ አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ፣ ሰላማዊ በሆነ መንገድ ኢትዮጵያውያንን ለመብታቸዉና ለነጻነታቸዉ የማደራጀት ስራዉን ቀጥሏል። ከዚህም የተነሳ የአንድነት ፓርቲ ሜዳዉን ሙሉ ለሙሉ ለገዢዉ ፓርቲ ባለመልቀቁ፣ አገዛዙ በሚመጣዉ የ2002 ዓ.ም ምርጫ (ምርጫዉ ፍትሃዊና ነጻ ከሆነ ) ትልቅ ሽንፈት እንደሚያጋጠመዉ ከወዲሁ ተረድቷል።

ስለዚህ ከምርጫዉ በፊት የአንድነት ፓርቲን ማዳከም ዋነኛና ብቸኛ ታክቲኩ በማድረግ ፣ በአንድነት ላይ የሚያደርገዉን አፈና ተያይዞታል። ድርጅቱን ለመበታተን ብሎ የድርጅቱ አንጋፋና ቆራጥ መሪ የሆኑትን ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ በግፍ አስሮ ከአራት ወር በላይ በጨለማ ቤት ዉስጥ እንዲቀመጡ አድርጓል። «ታጋይ ቢታሰር ትግል አይታሰርም» በሚለዉ መርህ የአንድነት ፓርቲ ግን በተለያዩ አቅጣጫዎች የተቃጡበትን የፕሮፖጋንዳን ዘመቻዎችን ሁሉ በመመከት፣ ልዩነቶቹን ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድና በሰለጠነ መልኩ በመፍታት፣ ሕዝቡን የማደረጀትና የማንቃት ሥራዉን አላቋረጠም። ኢትዮጵያዉያን በወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ላይ የደረሰዉን ግፍ እንዲያወቁና እኝህ መሪ በከፈቱት በር ገብተዉ ትግሉን እንዲያጧጥፉ ለማድረግ እንቅስቃሴዎችን እያደረገ ነዉ።

ከእንስቃሴዎች አካላት አንዱ ሕዝባዊ ስብሰባዎችን በማዘጋጀት ከሕዝቡ ጋር መወያየት ነዉ። በዚህ መሰረት የአንድነት ፓርቲ ፣ ግንቦት 15 ቀን 2001 ከሕዝቡ ጋር ለመወያየት ይረዳዉ ዘንድ በአዲስ አበባ የመብራት ኃያል አዳራሽን መጠቀም እንዲቻል፣ የአዳራሹን ባላቤቶች አነጋገረ። ስብሰባም እንደሚያደርግ ለመንግስት ባለሥልጣናት አሳወቀ።

አዳራሹ እንዳልተያዘና በዚያ ቀን መጠቀም እንደሚቻል ከባላቤቶቹ ለማወቅ ተቻለ። ከጥቂት ቀናት በኋላ ለአዳራሹ ክፍያ ለመክፈል ሲኬድ ከመንግስት ፍቃድ አምጡ ሲባል፣ የመንግስት ባለሥልጣናት ሲጠየቁ ደግሞ ከአዳራሹ ባለቤቶች የተከራያችሁበት ወረቀት አምጡ ተባለ። እንዲህ እየተባለ ከብዙ መንገላታት በኋላ ጭራሹኑ አዳራሹን መጠቀም እንደማይቻልና ሌሎች

እንደያዙት ከአዳራሹ ባላቤቶች ተነገረ። ይሄ ሁሉ እንግዲህ የሚያሳያዉ ገዢዉ ፓርቲ ምን ያህል የአንድነት ፓርቲን እንደሚፈራና ፓርቲዉን ለማዳከም የሚጠቀምባቸዉን የተለያዩ ተንኮሎችና ጨዋታዎችን ነዉ።

የአንድነት ፓርቲ ግን ከእንቅስቃሴዉ አልተገደበም። ተስፋ ቆርጦ ቁጭ አላለም። ሜዳዉን ለወያኔ-ኢሕአዴግ ብቻ አለቀቀም። የድርጅቱ ላእላይ ምክር ቤት እየሆነ ያለዉ ሁሉ የትግሉ አካል እንደሆነ ተረድቶ በጉዳዩ ከመከረ በኋላ ሕዝባዊዉ ስብሰባ በመስቀል አደባባይ እንዲሆን ወሰነ። የአመራር አባላቱም ግንቦት 10 ቀን 2001 ዓ.ም፣ በግንቦት 23 ቀን 2001 በመስቀል አደባባይ ከጠዋቱ 3:00 ጀምሮ ሕዝባዊ ስብሰባ ለማካሄድ ለሚመለከታቸዉ ባለሥልጣናት ደብዳቤ አስገቡ።

የአንድነት ፓርቲ የሚያደርገዉ ሰላማዊ ትንቅንቅ በእንዲህ ሁኔታ ላይ እያለ፣ «አመቺ ነዉ ብላቹህ በመረጣችሁት መሰብሰቢያ አዳራሽ ማካሄድ እንዳለባቹህ ታሞኖበታል» በሚል፣ ግንቦት 13 ቀን 2001 አቶ ማርቆስ ብዙነህ የሚባሉ የሰላማዊ ሰልፍና የሕዝባዊ ስብሰባ ማሳወቂያ ኦፊሰር በጻፉት ደብዳቤ፣ በመስቀል አደባባይ ስብሰባ ማድረግ እንደማይቻል ተገለጸ።

የወያኔ-ኢህአዴግ ባለሥልጣናት የተላከዉ ደብዳቤ የከተማዉ ወይም የአወራጃዉ አስተዳደር ጽ/ቤት ሃላፊነትን የሚገልጸዉ አዋጅ ቁጠር 3/1998 አንቀጽ 6 ንኡስ አንቀጽ አንድና ሁለትን በመጠቀስ ነበር፣ የአንድነት ፓርቲ የጠራዉ ስብሰባ እንዳይደረግ የከለከለዉ።

በባለስልጣኑ የተጠቀሰዉ የሕግ አንቀጽ ግን ዜጎች ሰላማዊ ሰልፍ ሆነ ሕዝባዊ ስብሰባዎች በየትኛዉም ቦታ ማካሄድ እንደሚችሉ የደነገገ ሲሆን፣ ገዢዉ ፓርቲ በመሰለዉ መልኩ ሕግን እያጣመመ በሕግ ስም የዜጎችን መብት እየረገጠና ህግን መቀለጃ እያደረገ እንዳለ በግልጽ የሚያሳይ ክስተት እንደሆነ የሚያሳይ ነዉ።

ለግንዛቤ ይረዳ ዘንድ በባለሥልጣናቱ የተጠቀሰዉን የሕግ አንቀጽ እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡

> *«አዋጅ ቀጠር 3/1998 አንቀጽ 6 ፡*
>
> *ንኡስ አንቀጽ 1 - የከተማዉ ወይም የአወራጃዉ አስተዳደር ጽ/ቤት የሰላማዊ ሰልፍ ወይም ሕዝባዊ የፖለቲከ ስብሰባ ጥያቄ በጽሁፍ ሲቀርብለት ሰላምን ከማስፈን፣ ጸጥታን ከማስጠበቅና የሕዝቡን ዕለታዊ ኑሮ እንዳይሰናከል ከማድረግ አንጻር አሰፈላጊዉን ዝግጅት ሁሉ የማድረግ ሃላፊነት አለበት።*
>
> *ንኡስ አንቀጽ 2- የከተማዉ ወይም የአወራጃዉ አስተዳደር ጽ/ቤት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ንኡስ አንቀጽ 1 የተመለከቱትን ሁኔታዎች በማገናዘብ በሌላ ጊዜ ወይም በሌላ ስፍራ ቢደረግ ይሻላል የሚል አስተያየት ካለዉ ምክንያቱን በመግለጽ ይህንኑ ጥያቄዉ በደረሰዉ በ 12 ሰዓት ዉስጥ በጽሁፍ ለአዘጋጁ የማሳወቅ ሃላፊነት አለበት። **ሆኖም የከተማዉ ወይም የአወራጃዉ አስተዳደር ጽ/ቤት ሰላማዊዉ ሰልፉ ወይም ሕዝባዊ የፖለቲካ ስብሰባዉ ምን ጊዜም በየትኛዉም ቦታ ሊካሄድ አይችለም ማለት አይችለም።»***

ይህ ከላይ የተጠቀሰዉ የሕግ አንቀጽ በግልጽ እንደሚያሳየዉ ዜጎች ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግና የመሰብሰብ መብታ እንዳላቸዉ ፣ የክልሉ አስተዳዳሪዎች ሚና የዜጎችን መብት ማገድ ሳይሆን የዜጎች መብት እንዲከበር ማገዝ እንደሆነ ያሳያል።

እንደዚያም ሆኖ ግን ባለሥልጣናቱ የተለያዩ ምክንያቶች እየሰጡ የአንድነት ፓርቲ ስብሰባዎችን እንዳያደርግና ሕዝቡን የበለጠ እንዳያደራጅ፣ ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ ትልቅ መሰናክል እየፈጠሩበት እንደሚገኙ የሚያሳይ ነዉ።

ሁኔታዉ እንዲህ እንዳለ፣ የአንድነት ፓርቲ ግን ያለዉን ቁርጠኝነት የበለጠ እየጨመረና የተደቀኑትን መሰናክሎች እያለፈ ሕዝብን የማደራጀት ሥራዉን የበለጠ ለመስራት እንደተዘጋጀ ለማወቅ ችለናል። አዲስ አበባን ጨምሮ በበርካታ ክልሎች የተለያዩ ሕዝባዊ ስብሰባዎችና ሰላማዊ ሰልፎች፣ በድፍረትና በቁርጠኝነት የማድረግ እቅድ እንዳለዉ ያረጋገጥን ሲሆን፣ የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ጉዳይንም የመጀመሪያና ማእከላዊ ትልቅ ትኩረቱ አድርጎ እየተንቀሳቀሰ እንደሆነና ወደፊትም እንደሚንቀሳቀስ ከአመራር አባላቱ ለመረዳት ችለናል።

የአንድነት ፓርቲ ከዚህ በፊት በአዲስ አበባ ከተማ ከምርጫ ዘጠና ሰባት በኋላ የመጀምሪያ የሆኑትን ሰላማዊ ሰልፍና ሕዝባዊ ስብሰባ ማድረጉና ፈር ቀዳጅ መሆኑ ይታወሳል።

እስከአሁን ድረስ የተደረጉት ሥራዎች በቀላሉ የተሰሩ ሥራዎች እንዳልሆኑ የተናገሩት አንድ የአንድነት አመራር አባል «ከዚህ በፊት የነበሩ መሰናክሎችን እንዳለፍን ሁሉ፣ በቁርጠኝነት፣ በትጋት፣ በወኔና በቅንነት ከሕዝቡ ጋር ሆነን ከሰራን፣ ወያኔ-ኢሕአዴግ ዛሬ ያስቀመጠዉንና ነገ የሚያስቀመጠዉን መሰናክሎች ማለፍ እንችላለን» ሲሉ አረጋገጠዋል። «የሕዝብ ኃይልን መቋቋም የሚችል ማንም ኃይል የለም» በማለትም እኚሁ የአመራር አባል ከሕዝቡ ጋር ሆኖ ሕዝብን እያደራጁ ፣ ሕዝብ በራሱ ተማምኖ፣ ለመብቱ እንዲንቀሳቀስ ከማድረግ ዉጭ ሌላ አማራጭ እንደሌለ አስረድተዋል።

የአንድነት ፓርቲ ከመስቀል አደባባይ ሕዝባዊ ስብሰባ መከልከል በኋላ የሚወስዳቸዉን እርምጃዎች ተከታትለን እንደምናቀርብ እየገለጽን ጊዜዉ ፈታኝ ጊዜ እንደመሆኑ ፣ ኢትዮጵያዉያን ሁሉ የበለጠ ከአንድነት ጋር እንዲሰለፉና የሰላማዊዉ ትግል አገር ሆነዉ በጽናት እንዲታገሉ ጥሪ እናቀርባለን።